መልእክት ሁለት

## በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የእግዚአብሔርን ጸጋ መለማመድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ኤፌ. 1፥10; 3፥9; 1 ጢሞ. 1፥4; ገላ. 6፥18; 1 ቆሮ. 15፥10; 2 ጴጥ. 3፥18

**I. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ የክርስቶስ አካል፣ ቤተ ክርስቲያን ይሆኑ ዘንድ ከእርሱ ጋር እንደ አንድ እንዲጋጠሙ፣ በእርሱ እንዲሞሉና በእርሱ እንዲያዙ፣ በምድር ላይ ከእርሱ ጋር አንድ ሕይወታዊ አካል እንዲሆኑ፣ ሕይወታቸውና ሁሉ ነገራቸው ለመሆን ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ወደ ውስጣቸው ያድል ዘንድ የሰዎችን ቡድን ማግኘት ነው—ኤፌ. 1፥3-23፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መስመር ነው—ቁ. 10፤ 3፥9።

ለ. የቅዱሳት መጻሕፍት ፍቺ በአብርሆቱ ሥር በዚህ ማዕከላዊ መስመር ጥብቅ በሆነ መልኩ መገዛት አለበት—ሉቃ. 24፥27፣32፣44።

ሐ. ሊተኮርበት፣ አጽንኦት ሊሰጠው እና ለሌሎች ሊገለገል የሚገባው አንድ ነገር የእግዚአብሔር የአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ነው—1 ጢሞ. 1፥4።

መ. የክርስቲያን ሕይወት ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የሆነ ሕይወት ነው—2 ቆሮ. 5፥14-15።

**II. "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን"—ገላ. 6፥18፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትኩረት ክርስቶስ ዛሬ በመንፈሳችን ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ነው—ቁ. 18፦

1. መንፈስ ያደረበት ዳግም የተወለደው መንፈሳችን የእግዚአብሔር የበረከት ተስፋ ትኩረት ነው—ዮሐ. 3፥6፤ ሮሜ 8፥10፤ 15፥29፤ ኤፌ. 1፥3።
2. ሁሉን-ያካተተው መንፈስ የተትረፈረፈ አቅርቦት የሆነው የጌታ ጸጋ ከመንፈሳችን ጋር ሊሆን ያስፈልገናል—ፊልጵ 1፥19፤ 2 ጢሞ. 4፥22።

ለ. የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ በመንፈሳችን መንቀሳቀስ የምንደሰተው የሦስታንዱ አምላክ (በወልድ አካል የለበሰውና ሕይወት እንደሚሠጠው መንፈስ እውን የሆነው) የተትረፈረፈ አቅርቦት ነው—ዮሐ. 1፥14፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ጢሞ. 4፥22፤ ፊልሞና 25፦

1. ጸጋ እግዚአብሔር አብ እንደ መንፈስ እውን በሆነው በወልድ አካል ለብሶ ነው፤ በስተመጨረሻ መንፈስ ጸጋ ነው—ዕብ. 10፥29።
2. የሦስታንዱ አምላክ ከፍተኛ-መጨረሻ-ምርጥ መጠናቀቅ የሆነው ይህ ጸጋ አሁን በመንፈሳችን ይኖራል—ፊልጵ. 4፥23።
3. መንፈሳችን ጸጋን ልንለማመድበት የምንችልበት ብቸኛው ስፍራ ነው—2 ጢሞ. 4፥22።
4. ለጌታ እንደ ራስ እና እንደ ንጉሥ እውቅና በመስጠት፣ የእርሱን ስፍራ በማክበር፣ ሥልጣኑን በማክበር እና የጸጋው ዙፋን በመንፈሳችን ውስጥ መሆኑን በማየት ጸጋን ለመቀበልና ለመደሰት ወደ መንፈሳችን መዞር እና በዚያ መቆየት ያስፈልገናል—ገላ. 6፥18፤ ዕብ. 4፥16።

ሐ. እንደ የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈሳችን የጌታችንን ጸጋ የምንቀበልና የምንደሰት ሰዎች መሆን አለብን—2 ቆሮ. 13፥14፤ ፊልሞና 25፦

1. ክርስቶስን እንደ የጸጋ መንፈስ መቀበል የሕይወት ዘመን ሁሉ፣ የማያቋርጥ ጉዳይ ነው—ዮሐ. 1፥16፤ ራእ. 22፥21።
2. ዕለት ዕለት እግዚአብሔር የጸጋን መንፈስ አቅርቦት አትረፍርፎ ሲሰጥና እኛም የጸጋን መንፈስ ባለማቋረጥ ስንቀበል ሳለን ድንቅ መለኮታዊ መተላለፍ መከናወን አለበት—ገላ. 3፥2-5፤ ዮሐ. 3፥34።
3. ሁሉን-ያካተተውን ሕይወት የሚሠጠውን የጸጋ መንፈስ አቅርቦት ለመቀበል ለሰማያዊው መተላለፍ ራሳችንን የመክፈት መንገዱ ለመጸለይ እና ጌታን ለመጥራት መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ነው—1 ተሰ. 5፥16-18፤ ሮሜ 10፥12-13።
4. በሂደት ያለፈውን እና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ ጸጋችን ስንቀበል እና ስንደሰት ቀስ በቀስ በሕይወት ከእርሱ ጋር አንድ እንሆናለን፤ እርሱ ቅንብራችን ይሆናል፣ እኛም መገለጡ እንሆናለን—2 ቆሮ. 1፥12፤ 12፥9።

**III. "ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም...ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም"— 1 ቆሮ. 15፥10፦**

ሀ. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡10 ሦስት ጊዜ የተጠቀሰው ጸጋ በትንሣኤ እንኖር ዘንድ ሕይወታችንና የሕይወት አቅርቦታችን እንዲሆን በሂደት ያለፈውን ሦስታንዱን አምላክ በትንሣኤ ወደ ውስጣችን ለማምጣት ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ሕይወት የሚሠጥ መንፈስ መሆኑ ነው (ቁ. 45)፦

1. ጸጋ ሦስታንዱ አምላክ ሕይወት እና ሁሉ ነገራችን መሆኑ ነው—ዮሐ. 1፡17፤ ገላ. 2፡21።
2. ከኃጢአተኞች ዋና የነበረው የጠርሴሱ ሳውል (1 ጢሞ. 1፡15-16) ከሐዋርያት ሁሉ በላይ አብልጦ በመድከም ቀዳሚ ሐዋርያ የሆነው በዚህ ጸጋ ነው።
3. በዚህ ጸጋ የሆነው የጳውሎስ አገልግሎት እና ኑሮ ለክርስቶስ ትንሣኤ የማይካዱ ምስክሮች ናቸው—2 ቆሮ. 1፡12፤ 12፡9።

ለ. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡10 *የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም* በገላትያ 2፡20 ካለው *ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ* ከሚለው ጋር እኩል ነው፤ ይህ የሚያሳየው ክርስቶስ ራሱ የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑን—እግዚአብሔር ራሱ በሐዋርያው በኩል *መሥራቱን*—ነው፦

1. ሐዋርያው ጳውሎስን ያነሳሳው እና በእርሱ የሠራው ጸጋ የሆነ ጉዳይ ወይም የሆነ ነገር ሳይሆን ሕያው ማንነት፣ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ፣ በሐዋርያው እንደ ሁሉ ነገሩ ያደረው ሁሉን-ያካተተው ሕይወት የሚሠጠው መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር አብ አካል መልበስ ነው።
2. ይህ በፊልጵስዩስ 4፡13 "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" ከሚለው ከጳውሎስ አዋጅ ጋር ይገጣጠማል፦
   ሀ. በፊልጵስዩስ 4፡13 *በክርስቶስ* የሚለው ቃል ሕይወት የሚሠጥ መንፈስ የሆነውን ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ያመለክታል።
   ለ. እንዲህ ባለ ክርስቶስ ጳውሎስ ሁሉን ነገሮች ለማድረግ ኃይል አገኘ፤ ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

## IV. "በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ...እደጉ"—2 ጴጥ. 3፡18፦

ሀ. ጸጋ ለእኛና በእኛ ውስጥ ሦስታንዱ አምላክ ሕይወት እና የሕይወት አቅርቦት ሲሆንልን ነው፤ በጸጋ ማደግ በዚህ ውስጣዊ የሕይወት አቅርቦት ምንጭ ማደግ ነው—1 ጴጥ. 5፡10።

ለ. ጸጋ እግዚአብሔር በተሠግዎ፣ በሞት፣ በትንሣኤ እና በዕርገት ሂደት ማለፉ ነው፤ እነዚህ የጸጋ ንጥረ-ነገሮች ሁሉ ከእኛ ጋር አንድ ለመሆን በእኛ ውስጥ ናቸው—ፊልጵ. 4፡23፦

1. ከእኛ ጋር አንድ እንዲሆን፣ እንዲያድነን፣ በእኛ ውስጥ ቤቱን እንዲሠራ እና በእኛ ውስጥ እንዲሠራ፣ ጸጋ እንደ ሕይወታችን እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ በጸጋ ማደግ በእግዚአብሔር መጨመር ማደግ ነው—ቆላ. 2፡19።
2. እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይቆይ ዘንድ እና ራሱን ከእኛ ጋር አንድ ያደርግ ዘንድ ጸጋ የእግዚአብሔር ጉብኝት ነው፤ የዛሬና የወደፊት ዘላለም ለሆነው ክብሩ እንዲህ ባለ ጸጋ ማደግ ያስፈልገናል—ራእ. 22፡21።

*© 2022 Living Stream Ministry*